# ምን ይጠበቃል፡- የተንቀሳቃሽ የክትባት ክሊኒክ የመጎብኘት ጽሁፍ

ተንቀሳቃሽ የክትባቶች ክሊኒኮች የ COVID-19 ክትባትን ወደ እርስዎ እና ማህበረሰብዎ ያመጣሉ። ይህ ቪድዮ ተንቀሳቃሽ የክትባት ክሊኒክን ሲጎበኙ ሊጠብቁ የሚችሉት ነገር ያሳዮታል።

ወደ ተንቀሳቃሽ ክሊኒኩ ሲደርሱ ለክትባት ቀጠሮዎ ተቀባይ ጋር ይመዘገባሉ።

*[ተቀባይ] ሰላም! ጥሩ፣ ዛሬ እንዲመዘገቡ ኢደርግዎታለው። የኢያትዎ ስም ማን ነው?*

የተደራሽነት ወይም የቋንቋ እርዳታዎችን ከፈለጉ እባክዎን ያሳውቋቸው። ተንቀሳቃሽ የክትባት ክሊኒክ ብዙውን ጊዜ ያለቀጠሮ ክፍት ናቸው፣ ስለሆነም ጓደኛ ይዘው ይምጡ!

*[ተቀባይ] ለመሄድ ዝግጁ ነዎት፤ ወደ ወረፋው መሄድ ይችላሉ።*

ተራዎን በቀጥታ ከአውቶቡስ ውጭ ወይም በአውቶቡሱ ውስጥ ባለው የመጠበቅያ ቦታ ውስጥ ይጠብቁ።

ለመከተብ የእርስዎ ተራ ሲሆን፣ ከህክምና ባለሙያ ጋር በክትባት ጣቢያው ውስጥ ይቀመጡ። የበለጠ ግላዊነት ከፈለጉ መሸፈኛዎች አሉ።

*[የህክምና ባለሙያ] ስምዎትን ሊነግሩኝ ይችላሉ?*

የህክምና ባለሙያው መረጃዎን ከእርስዎ ጋር ይከልሳል እናም ስለ ክትባቱ ያልዎትን ማንኛውንም ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ።

ክትባቱን ለመስጠት የህክምና ባለሙያው የላይኛው ክንድዎን ማመቻቸት ያስፈልገዋል።

አንዴ ከተከተቡ በኋላ፣ ከአውቶቡስ ይወጣሉ።

*[ሰራተኛ]ሰላም። ስለመጡ በጣም እናመሰግናለን። ክትባት ስለወሰዱ እናመሰግናለን። አሁን ደግሞ በዚህ አካባቢ እዚህ ጋር ለ 15 ደቂቃ ያህል ለክትትል እንዲጠብቁ  እንፈልጋለን።*

በክትትል ቦታ ውስጥ ለ 15 ደቂቃዎች ይቀመጣሉ። እናም ሰራተኛው ጥሩ ስሜት ካልተሰማዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎት ያብራራል። ጥሩ ስሜት ካልተሰማዎት እንደ ነርሶች ወይም እንደ ድንገተኛ የሕክምና ባለሙያዎች ያሉ የሰለጠኑ  ሠራተኞች በቦታው ላይ ናቸው።

15 ደቂቃዎችዎ ካለፉ በኋላ፣ ጨርሰዋል!

ክትባት ስለወሰዱ እናመሰግናለን።

ስለ COVID-19 ክትባት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ ወይም ድረገጻችንን ይጎብኙ። https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/vaccine/index.html

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

6/17/21 (Amharic)

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፣ በዚህ ይደውሉ፡-  651-201-4989*